# ★ ዴሞክራሲያ ★

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

**ቅጽ** 35 **ቁጥር** 2 **ኅዳር** 2002 **ዓ.ም.**


## ችግርን መቀፍቀፍ፥ ረሃብን ማምረት

ሰሞኑን አገራችን በድርቅ እንደምትጠቃ፥ ረሃብ፥ ጠኔ እንደሚጎበኛት አስከትሎም እንደተለተመደው አስቸኳይ የምግብ እርዳታ ካልተደረገ በሚሊዮን የሚቆጠረው ሕዝባችን በዚሁ በረሃብ ህይወቱ ባሰቃቂ ሁኔታ እንደሚያልፍ እየተነገረን ነው፡፡ የዛሬ 35 እና የዛሬ 27 ዓመታት የዓለም ሕዝብ በቴሌቪዥን መስኮቶች የተመለከታቸው አሰቃቂ ትዕይንቶች አሁንም በድጋሚ ሊታዩ የሚችሉበት ሁኔታ እያቆበቆበ መሆኑ እየተገለጸ ነው፡፡ በ1965 እና በ1976 ያየናቸው የተጣበቁ ሰውነቶች፥ የተኮማተሩ አንጀቶች፥ ቆዳን ፈርጥቀው የወጡ አጥንቶች፥ መራራ ትዝታዎች ናቸው፡፡ እርጋፊ እህሎችን ከመሬት ሲለቅሙ፥ ከብት እንኳን የማይበላውን አረም ሲበሉ፥ ጥቂት የሚቀመስ ለማግኘት ረዥም መንገድ ሲጓዙ፥ በየመንገዱ ጉልበት ተስኗቸው ሲወድቁና የአውሬ ሲሳይ ሲሆኑ ያየናቸው ዜጎቻችን አሁንም አንጀታችንን የሚያባቡ፥ የደም ግፊታችንን የሚጨምሩ፥ የደም ስራችንን የሚነዝሩ ናቸው፡፡

ኢትዮጵያና ድርቅን፥ ኢትዮጵያና ረሃብን፥ ኢትዮጵያና ምጽዋት ተቀባይነትን አንድ ላይ በማስቀመጥ በየአሥር ዓመቱ በዓለም የዜና ማሰራጫዎች የሚደለቀው የዜና ጋጋታ የእኛ ኢትዮጵያውያንን አንጀት ማሳረሩና አንገት ማስደፋቱ አልቀረም፡፡ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ረሃብ የወገኖቻችንን ህይወት መቅጠፍ በጀመረበት ባሁኑ ሰዓት ሥልጣኑን ከጨበጠው ከከፋፋዩ ፀረ ኢትዮጵያ የወያኔ ቡድን በኪራይ ለም መሬቶች እየተሰጣቸው የአመረቱትን ምርት ከረሃብተኛው አፍ እየነጠቁ ወደ አገራቸው ሲወስዱ ስናይ የበለጠ መብገናችንና መንገብገባችን አልቀረም፡፡

በንጉሡ ጊዜ የተራበው ሕዝብ ቁጥር 1.2 ሚሊዮን ነበር፡፡ ችግሩ ለረዥም ጊዜ በመደበቁና እርዳታው በተገበው መንገድ በፍጥነት ባለመድረሱ ከ80 ሺ በላይ የሆነ ወገናችን በረሃብ አልቋል፡፡ ረሃቡ የአስከተለው እልቂት እንደምክንያት ሆኖ የየካቲት 66ቱን እንቅስቃሴ ለመቀስቀስና በኋላም የንጉሡን ሥርዓት ለማውረድ አስተዋጽኦ ያደረገ ቢሆንም በሥልጣን የተተካው ደርግ ከ10 አመት በኋላ ሕዝቡን እንደገና ለሌላ የረሃብ አልቂት ዳርጓል፡፡ በ1976 እና 77 ዓመተ ምህረት በረሃብ ከተጠቃው ከ 6.5 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን በላይ የሚቆጠረው እንደቅጠል መርገፉን እናስታውሳለን፡፡ በደርግ እግር በተተካው በአምባገነኑና ከፋፋዩ ቡድን በወያኔ ዘመን ደግሞ ወደ 14 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝብ ለረሃብና ለእልቂት እየተዳረገ መሆኑ በሰፊው እየተነገረ ነው፡፡ መንግሥት ተብየው ሲጋለጥ ያመነው 6.5 ሚሊዮን ብቻ ቢሆንም ባሁኑ ወቅት ላለፉት ዓመታት በቋሚነት የእህል እርዳታ እየተሰጠ ያለውን ወደ 7.5 ሚሊዮን የሚሆነውን ሕዝብ ጨምሮ ባጠቃላይ እርዳታ የሚያስፈልገው ወገን ቁጥር ወደ 14 ሚሊዮን መድረሱ ተረጋግጧል፡፡

ኢትዮጵያንና ረሃብን እንዲሁም ኢትዮጵያንና ድርቅን አዛምደው የሚያዩ አንዳንድ የባዕዳን ኃይሎች አገራችን በአየር ንብረትም ሆነ በተፈጥሮ ሀብት ያልታዳለች ስለሆነ ምንጊዜም ከረሃብና ከችግር ከጠኔና ከእልቂት ልታመልጥ አትችልምና በየጊዜው የምጽዋት እህል ሊቸራት ይገባል ይላሉ፡፡ ወያኔም በሁኔታዎች መጋለጥ ምክንያት ላመነው የ6.5 ሚሊዮን ሕዝብ የረሃብ ሰለባ መሆን

ምክንያት የተፈጥሮ አየር መዛባትና የዝናም እጥረት ነው እንጂ የቡድኑ ኃላፊነት እንዳልሆነ በተደጋጋሚ ሲለፍፍ ተደምጧል፡፡

ሀገራችን ለምን የድርቅና የረሃብ ሰለባ ሆነች? የሚለው ጥያቄ መሠረታዊ ነው፡፡ የአየር ንብረት መዛባት ለድርቅና ለረሃብ ብሎም ለእልቂት እንደምክንያት በየጊዜው ቢቀርብም በድርቅ ምክንያት ረሃብም ሆነ እልቂት መኖር እንደሌለበት ግልጽ ነው፡፡ በየወቅቱ በዚህ ላይ ወያኔ የሚያደርገው ልፈፋ እኩይ ተግባሩን ለመደበቅና ከኃላፊነት ለመሸሽ የሚያደርገው ማወናበድ እንጂ ሐቁ ከዚህ የተለየ ነው፡፡ የአየር ንብረት መዛባት በየወቅቱ የሚጎበኛቸው ወይም አብዛኛው የአገራቸው ክፍል በበረሃ የተሸፈነ ድርቅ የሚያጠቃቸው አገሮች በድርቅ ምክንያት ሕዝባቸው ለረሃብ ሲዳረግ ወይም በረሃብ ምክንያት እልቂት ሲከሰት በተለይ በ21ኛው ክፍለ ዘመን እየታየ አይደለም፡፡ ሌሎችም ቀደም ብሎ በድርቅና በረሃብ ሲጠቁ የነበሩ አገሮች በቂ የእርሻ ሰብል ለማምረት በነደፉት ትክክለኛ ፓሊሲና በተግባር ባዋሏቸው ዘዴዎች ምክንያት ዛሬ በእነዚህ አገሮች ረሃብ ቀርቶ የምግብ እጥረት እንኳ ጥያቄ የማይሆንበት ሁኔታ ውስጥ ገብተዋል፡፡ ቻይና፥ ህንድ፥ ባንግላዴሽ ፤ ቦትስዋናና መሰል አገሮች በየጊዜው በድርቅ የሚጠቁ አገሮች የነበሩ ቢሆንም ረሃብ የሚባለው ከጎበኛቸው ረጅም ጊዜ ሆኖታል፡፡

በአየር ንብረት መዛባት ምክንያት የሚደርስ ድርቅ የእህል ምርት መቀነስን ሊያስከትል እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ከዚህ በፊት በአገራችን የነበሩትም የረሃብ እልቂቶች የመጡት በድርቅ ምክንያት መሆኑ አከራካሪ አይደለም፡፡ ድርቅ አገራችንን በየጊዜው ይጎበኛታል፡፡ እንዲያውም እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ2034 በኢትዮጵያ ድርቅ የዘወትር ክስተት እንደሚሆን ማለትም በአራት አመት ጊዜ ውስጥ ሶስቱ አመቶች የድርቅ አመቶች እንደሚሆኑ አንዳንድ ባለሙያዎች በጥናት ላይ የተመሠረተ ግምት ይሰጣሉ፡፡ በአንዳንድ ወቅቶች በአንዳንድ አካባቢዎች ተከስቶ የነበረው ድርቅ የእህል ምርት መጠንን እንዲቀንስ ማድረጉ ግልጽ ቢሆንም አገራችን ካላት የተፈጥሮ ሀብት የተነሳ ረሃብና እልቂት ሊከሰቱም ሆነ ሊታዩ ባልተገባቸው ነበር፡፡ በተለይም የአፍሪካ የዳቦ ቅርጫት እየተባለች የምትጠራውና የራሷን ሕዝብ ቀርቶ ሌሎችን አገሮች የመመገብ ብቃት አላት እየተባለ በተደጋጋሚ ማረጋገጫ የተሰጣት አገራችን በድርቅ ዘመን ሕዝቧን መመገብ እያቃታትና ዘወትር የባዕድ ተመጽዋች ሆና መገኘቷ ለእኛ ለኢትዮጵያውያን አሳፋሪና ዘግናኝ ክስተት ነው፡፡

ከሌሎች አገሮች ተመክሮዎች በግልጽ ለመረዳት እንደሚቻለው በእርሻ ምርት መቀነስ ምክንያት ሊደርስ የሚችለውን ረሃብና እልቂት በሁለት መንገድ መወጣት ይቻላል፡፡ አንደኛው አገሪቱ ውስጥ ያለውን የእርሻ ምርት በመጨመር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የአርሶ አደሩን በተለይም በረሃብ አለንጋ የሚጠቃውን ወገን የገቢ መጠን ማሳደግ ነው፡፡ የገቢ አቅሙ የሚፈቅደለት አርሶ አደር በድርቅ ወር የሚያመርተው እህል ቢቀንስ ወይ ቢቋረጥ በሸመታ ችግሩን ሊወጣ ይችላል፡፡ ይህ ግን የኢኮኖሚ እድገትን፥ የትራንስፖርት አገልግሎት መስፋፋትና፥ የሕዝብን ነፃና ያልተገደበ ከቦታ ወደ ቦታ ዝውውርን ይጠይቃል፡፡

የመንግሥቱን ሥልጣን በያዘው ክፍል ተገቢ የሆነ ትኩረት ከተሰጠውና ሰፊና ጥልቀት ያለው ርብርቦሽ ከተደረገበት በአገራችን የእርሻ ምርትን መጠን ለመጨመር አዳጋች ሊሆን እንደማይችል ግልጽ ነው፡፡ አገራችን በተፈጥሮ ሀብታም ናት፡፡ አፈሯ ለእርሻ ተስማሚ ነው፡፡ ከኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት ውስጥ 70 ከመቶ የሚሆነው መታረስ እንደሚችል ሲገመት እስካሁን የሚታረሰው ከ10 እስከ 11 ከመቶ ብቻ ነው፡፡ በአንዳንድ ወቅቶች በአንዳንድ ቦታዎች የዝናም መቀነስና እልቂትን ያስከተለ ድርቅ ቢከሰትም አጠቃላይ በሆነ የውሃ መጠን አገራችን ደሃ አይደለችም፡፡ በኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት ላይ የሚፈሰው አጠቃላይ የውሃ መጠን በአመት በአማካይ 122 ቢሊዮን ሜትሪክ ቶን ይሆናል ተብሎ ይገመታል፡፡ ይህም የውሃ ሀብት ከብዙ አገሮች የውሃ ሀብት እንደሚበልጥ የተረጋገጠ ነው፡፡ አገራችን ለመስኖ እርሻዎች ሊጠቅሙ የሚችሉ በርካታ ወንዞችም አሏት፡፡ ግብጽ ከአባይ ወንዝ ከምታገኘው አጠቃላይ የውሃ መጠን ውስጥ 85 ከመቶ በላይ የምታገኘው ከአገራችን መንጭቶ አፈራችንንም አጋብሶ ይዞ ከሚሄደው ከጥቁር አባይ ነው፡፡ እንደ ተከዜ፥ አዋሽ፥ ዋቢ ሸበሌ፥ የመሳሰሉት ትላልቅ ወንዞች የወሃ ሀብቶቻችን ናቸው፡፡ በአንዳንድ ወቅት በአንዳንድ አካባቢዎች

በሚደርሰው ድርቅ ምክንያት መጠኑ ቢቀንስም በበርካታ የሀገራችን አካባቢዎች በቂ ዝናም ወቅቱን ጠብቆ ስለሚጥል የዝናም ወሃም ሌላ የወሃ ምንጭ ነው። ሀይቆችና የምድር ውስጥ የውሃ ጋኖችም በብዛት አሉ። የወሃ ሀብታችን ጥቅም ላይ ቢውል ማለትም ወንዞች ለመስኖ አገልግሎት ቢውሉ÷ የወሃ ሀብታችንን ለመገደብና ጥቅም ላይ ለማዋል ከፍተኛ ርብርብ ቢደረግ የአገራችን የእርሻ ምርት ውጤት ሕዝቦቿን በበቂ ከመመገብ አልፎ ለሌሎች አገሮች እንደሚተርፍ ምንም ጥርጥር የለም። የእርሻ ምርትና የአገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገት የተያያዘ ስለሆነ የእርሻ ምርት መጨመር ወይም መቀነስ የኢኮኖሚው እድገት መጨመር ወይም መቀነስ ላይ ተጽእኖ ያለው መሆኑን አዋቂዎች ይናገራሉ። በአገሪቱ ከሚመረተው ጠቅላላ ምርት ውስጥ የእርሻ ምርቱ ድርሻ 80 ከመቶ በሆነበት ሁኔታና 85 ከመቶ የሚሆነው ሕዝባችን በእርሻ ሥራ ላይ በተሰማራበት ሁኔታ የእርሻ ምርት መጠን ላገራችን ወሳኝ መሆኑ ይታያል። ስለሆነም በድርቅ ወቅት የሚደርሰው የእርሻ ምርት መቀነስ ከረሃቡ ባሻገር ኢኮኖሚውንም በጣም ወደኋላ ሊያስኬደው እንደሚችል ምንም ጥርጥር የለም።

አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ሥልጣን ከያዘ ጀምሮ በእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ወሰድኳቸው ያላቸው እርምጃዎች የሥልጣን ቁጥጥሩን ለማጥበቅ ጠቀሜታ የነበራቸው እንጂ የእርሻ ምርትን ለማሳደግ የተወሰዱ÷ የአርሶ አደሩን የኑሮና የገቢ ሁኔታ የሚያሻሽሉ ወይም ከድርቅና ከረሃብ የተነሳ የሚደርሰውን የሕዝብን እልቂት የሚከላከሉ አልነበረም። አርሶ አደሩ የሚያመርተው ምርት በጣም ዝቅተኛና ከእጅ ወደ አፍ በሆነ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ የወያኔ መረጃ ሳይቀር የሚያረጋግጡት ሐቅ ነው። እንዲያውም ላለፉት 19 ዓመታት በአማካይ 6.5 ሚሊዮን የሚሆን ሕዝባችን ራሱን መመገብ አቅጦት የነበረ መሆኑና በየአመቱ ከውጭ በሚገኝ የምጽዋት እህል ህይወቱ የቆየ መሆኑ በመረጃዎች ተረጋግጧል። ወያኔ የውሃ ሀብታችንን በእቅድና ለአርሶ አደሩ ጥቅም በሚሰጥ መልክ በስልት ሥራ ላይ ለማዋል የወሰደው እርምጃ እምብዛም ነው። በገፍ ከሚገኘው የውጭ ብድርና እርዳታ አንዳንድ ፕሮጀክቶችን የሠራ ቢሆንም ከሕዝባችን ፍላጎትና ጥቅም አንጻር ውጤት ያስገኘ ነበር ማለት አይቻልም። የአባይ ውሃን እንኳን እንደምሳሌ ብንወስድ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም ምን ያህል ትኩረት እንዳልተሰጠው መረዳት ይቻላል። ከላይ እንደተጠቀሰው ግብፅ ከ60 እስከ 80 በመቶ የሚሆነው የወሃ ሀብቷ የሚመጣው በአገራችን ከሚመነጨው ከአባይ ውሃ ሲሆን ኢትዮጵያ ከአባይ ውሃ ሀብት የምትጠቀመው ግን 1 ከመቶውን ብቻ ነው። ግብጽ እ.አ.አ በ1929 ከእንግሊዝ ቅኝ አገዛዝ ጋር ያደረገችውን ስምምነት መሠረት በማድረግ ሁለት ሶስተኛውን የአባይን ውሃ ለመጠቀምና በአባይ ላይ ድምፅን በድምፅ የመሻር (የቪቶ) ሥልጣን አለኝ ብላ እንዳሻት ስትፈነጭ ይህን ለመከላከልና ብሔራዊ ጥቅማችንን ለማስከበር ወያኔ የወሰደው እርምጃ የለም፤ አለም ቢባል እምብዛም ውጤት ያስገኘ አይደለም። የወሃ ሀብታችን ለሌላ መጠቀሚያ እየሆነ ሕዝባችን በድርቅና በረሃብ እንደቅጠል ሲረግፍ ማየት ቢዘገንነን÷ ቢያስቆጨንና ቢያስቆጣን ሊፈረድብን አይገባም። የዋና ዋና ወንዞቻችን ማለትም የአባይና የተከዜ÷ የባሮና አኮቦ÷ የጊቤና የኦሞ÷ የገናሌና የዳዋ÷ የዋቢ ሸበሌና የአዋሽ ወንዞችና የስምጥ ሸለቆ ሀይቆች በብዙ ሚሊዮን ሄክታር የሚገመት የእርሻ ቦታ በመስኖ ሊያለሙ እንደሚችሉ ባለሙያዎች ያረጋገጡት ጉዳይ ነው። ይህን ያህል የእርሻ ቦታ በመስኖ ቢለማ ሕዝባችን የምግብ ዋስትና አግኝቶ ድርቅና ረሃብ በሀገራችን የሚፈራና የማያቋርጥ መቅሰፍት ባልሆነ ነበር። ይህ ግን አልሆነም።

ሕዝባችን በየወቅቱ ከድርቅና ከረሃብ በተነሳ ችግር የሚደርስበት እልቂት ሊወገድ የሚችለው ወይም አገራችን ከተመጽዋች ተራ ወጥታ ራሷ መጽዋች እንድትሆን ለማድረግ የምትችለው የአርሶ አደሩ የገቢ መጠን እንዲያድግና የኑሮ ሁኔታው እንዲሻሻል ሲደረግ ነው። ይህ ሊሆን የሚችለው የእርሻው ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ መሠረታዊ ለውጥና ርብርብ ተደርጎ የእርሻ ምርት ወጤት እንዲያድግ ሲደረግ ብቻ ነው። እርሻ ለአገራችን ወሳኝ ነው። 85 ከመቶው የሆነው ሕዝባችን የሚተዳደረው በእርሻ፤ ከአገሪቱ ጠቅላላ የምርት ውጤት ውስጥ 47 ከመቶ የሚሆነው የሚገኘው ከእርሻ፤ 90 ከመቶው የሆነውን የውጭ ንግዳችንን የሚሸፍነው የእርሻ ውጤት ነው። ይህ በመሆኑም በድርቅና በረሃብ ሳቢያ የሚደርሰውን የወገኖቻችንን እልቂት ለመከላከልም ሆነ ኤኮኖሚያችንን ለማሳደግ የእርሻ ክፍለ አኮኖሚውን ማሳደግ ለአንድ መንግሥት የቅድሚያ እርምጃ በሆነ ነበር። በተቆራረጡና በየጊዜው እየጠበቡ በሚሄዱ የእርሻ መሬቶች ላይ የተመሠረተውን የአርሶ አደሩን

*የመሬት ይዞታ ለውጦና የእርሻውን ዘዴ አሻሽሎ አርሶ አደሩ የሚያመርተውን ሰብል እንዲያሳድግ ማድረግ፤ የመገናኛ መንገዶችን ማስፋፋት፤ አነስተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶችን ማቋቋም፤ የመሬትና የውሃ አጠቃቀም ሁኔታን ማሻሻል፤ ...ቅድሚያና ትኩረት የሚያስፈልጋቸው ተግባሮች ነበሩ። አምባገነኑ የወያኔ ሥርዓት ግን በዚህ ላይ ብዙ ደንታ የሚሰጠው ሆኖ አልተገኘም። ወያኔ ባለፉት ዓመታት ለእርሻ ልማት የመደበው የካፒታል ወጭ በተመሳሳይ ጊዜ ከሳህራ በታች ያሉ አገሮች ከመደቡት ወጭ ጋር ሲወዳደር በጣም አነስተኛ መሆኑን ባለሙያዎች በጥናታቸው አስፍረዋል። በአጠቃላይ የእርሻ ምርትን ለማሳደግ ወያኔ ያደረገው ጥረት በጣም ደካማ ነው ቢባል ከእውነት የራቀ አይደለም።*

*የእርሻ ምርትን ለማሻሻል መከናወን ከሚገባቸው ተግባሮች አንዱ የመሬት ይዞታን ማሻሻል ነው። ባሁኑ ወቅት የመሬት ባለቤትነት፥ ሀገሪቱን በማውደም ላይ ባለው በወያኔ ቁጥጥር ሥር ነው። በኢትዮጵያ ሁኔታ የእርሻ ምርትን ለማሳደግም ሆነ የአርሶ አደሩ ገቢም ከፍ ብሎ ኑሮው እንዲሻሻል ለማድረግ፥ አርሶ አደሩ የግል የመሬት ይዞታ መብቱ ሊረጋገጥለት ይገባል። መሬትን በግል በባለቤትነት መያዝ አለበት። በንጉሡ ጊዜ 35 ሚሊዮን የነበረው የሕዝብ ቁጥር በደርግ ጊዜ 55 ሚሊዮን አሁን ደግሞ 82 ሚሊዮን መድረሱ ይታወቃል። የሕዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በገጠር አርሶ አደሩ የሚያርሰው መሬት ስፋት እየተሸነሸነና እያነሰ ሄደ እንጂ እንዲጨምር የተደረገበት ሁኔታ የለም። የበሬ ግምባር በሚያህልና በተደጋጋሚ በታረሰና በማዳበሪያ በተጎዳ መሬት ላይ እርሻ ማከናወን የአየሩ ሁኔታ ተስማሚ ቢሆን እንኳ የምርቱ ውጤት አነስተኛ ሊሆን እንደሚችል ግልጽ ነው። የአርሶ አደሩን ምርት ለማሳደግ የእርሻ መሳሪያዎችን ከማሻሻል፥ ምርጥ ዘሮችን ጥቅም ላይ ከማዋል፥ ዘመናዊ የአስተራረስ ዘዴን ከመጠቀም በተጨማሪ የመሬት ይዞታን ማሻሻል እጅግ በጣም አስፈላጊና ወሳኝ ነው። አርሶ አደሩ ራሱንም ሆነ ቤተሰቦቹን ለመመገብና ለማስተዳደር እንዲያስችለው በቂ ስፋት ያለው የእርሻ መሬት እንዲኖረው ያስፈልጋል። ለዚህ በቅድሚያ መወሰድ የሚኖርበት እርምጃ አርሶ አደሩ የሚያርሰውን መሬት በባለቤትነት ሊይዝ የሚችልበት ሁኔታ መፍጠር ነው። መሬት በመንግሥት ቁጥጥር ሥር መሆኑ አርሶ አደሩ በመሬቱ ላይ ዋስትና እንዳይኖረው አድርጓል። አርሶ አደሩ በሌሎች የገቢውን መጠን ከፍ ሊያደርጉ በሚችሉ ልዩ ልዩ መስኮች ተሰማርቶ ኑሮውን እንዳያሻሽል ገድቧል። አርሶ አደሩ በመሬቱ የሚኖረው ባለቤትነት የተረጋገጠ ከሆነ መሬቱን አስመልክቶ ዋስትና ያገኛል። ቢሻው ያርሰዋል፥ ጠቃሚ መስሎ ካልታየው አከራይቶ ወይም በወለድ አግድ አስይዞ ሌላ መሬት ለማረስ ወይም ሌላ ሥራ ለመሥራት ይሄዳል። የኤኮኖሚ እድገት ሊገኝ የሚችለውም ሕዝባችን እንደልቡ የሚፈልገውን ሥራ እየሠራ ኑሮውን ለማሻሻል ሲችል ብቻ ነው። ባሁኑ ወቅት በገጠር ያለው ሕዝባችን ይህ መሠረታዊ የሆነ መብቱ በወያኔ ታግቶ ይገኛል።*

*ወያኔ የገጠርን መሬት በአገዛዙ ቁጥጥር ሥር እንዲሆን ያደረገው በሥልጣን ላይ ለመቆየት አርሶ አደሩን መቆጣጠር አስፈላጊና ወሳኝ ሆኖ ስላገኘው ነው። መሬትን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር በማድረግ አርሶ አደሩን የመንግሥት ጥገኛ ያደርጋል፤ ሊደርስ የሚችለውን ተቃውሞና እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ይችላል። የገበሬ ማኅበራትና የወያኔ ካድሬዎች በየገጠሩ የሚያከናውኑት የቁጥጥር ተግባር ይህንኑ የሚያረጋግጥ ነው። በተጨማሪም የመሬት ይዞታን በቁጥጥሩ ሥር በማዋል ወያኔ ሥልጣን ላይ ለመቆየት እየተጠቀመበት ላለው የዘር ክፍፍል አስፈላጊ ሆኖ አግኝቶታል። አርሶ አደሩ በመሬት ይዞታው የመንግሥት ጥገኛ ከሆነ ባለበት በዘር በተከፈለ ክልል ውስጥ ለመቆየት ይገደዳል። የሕዝብ ከቦታ ወደቦታ የመንቀሳቀስ ነፃነትን ይገደባል። የእርስ በርስ ግንኙነት፥ ትስስርና ውህደት እየመነመነ ይሄዳል። ይህም ለከፋፋዩ ወያኔ የሥልጣን ዕድሜ በጣም አስፈላጊ ሆኖለታል።*

*ረሃብና እልቂት በአገሪቱ ላይ እያንዣበቡ ባሉበት ወቅት ለአገርና ለሕዝብ ደንታ የሌለው ወያኔ የራሱን ካዝና ለማደለብ ለም የእርሻ መሬቶችን ለባዕድ መንግሥታትና ለውጭ ባለ ሀብቶች በኪራይ መልክ ቸብችቧል፥ አሁንም እየቸበቸበ ነው። እስካሁን ከ3 ሚሊዮን ሄክታር በላይ የሆነ መሬት ለባዕዳን ከ40 እስከ 90 አመት ለሆነ ጊዜ በኪራይ መልክ የሰጠ ሲሆን መሬትን የማከራየቱ ተግባር በስፋትና በብዛት እንደሚቀጥል የወያኔው ቁንጮ በትዕቢትና በድፍረት በተደጋጋሚ ተናገሯል።*

በሄክታር 15 የኢትዮጵያ ብር ሂሳብ በኪራይ ለባዕዳን የተሰጠው መሬት የሚገኘው በአብዛኛው ድርቅ በማያጠቃቸውና ለም በሆኑ አካባቢዎች ውስጥ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። መሬት በኪራይ መልክ የተሰጣቸው መንግሥታት ሳውዲ አረቢያ፥ ህንድ፥ ቻይና፥ የተባበረው አረብ ኤሚሬትና ከአውሮፓ የጀርመን ኩባንያዎች እንዲሁም እንደነ-አላሙዲ የመሳሰሉ የወያኔ ሸሪኮችና የጥቅም ተካፋዮች ሲሆኑ ባለሀብቶቹ በኪራይ ስንዴ፥ ገብስ፥ ሩዝ፥ በቆሎ፥ የቅባት እህሎች፥ አበባ፥ ሻይ ቡናና እንዲሁም ከእህል ዘር ለሚመረት ነዳጅ (ለባዮ ፊውል) የሚጠቅም አዝርዕት አምርተው ወደ አገራቸው ለማጓጓዝ አቅደዋል። እስራዔልና ሌሎች አገሮችም ለከብት እርባታ ለሌሎች እርሻ ነክ ሥራዎች መሬት በኪራይ ለማግኘት ፍላጎት እንዳላቸው ታውቋል። ባዕዳኑ ከአገራቸው ውጭ መሬትን ተከራይተው የእርሻ ምርት ለማምረት የፈለገቡት ምክንያት ርካሽ በሆነ የኪራይ ዋጋና ርካሽ በሆነ የሰው ጉልበት (የራሳቸውንም አርሶ አደር በማሰማራት ጭምር) በአነስተኛ ወጭ ምርቶችን አምርተው የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ነው። በተለይም በየጊዜው እየጨመረ የሄደው የእህል ዋጋ ብዙዎችን ያሳሰበ መሆኑ ግልጽ ነው። ከላይ ለመተንተን እንደሞከርነው፥ ሀገራችን በረሀብተኛ ጎራ ተፈርጃ ባለችበትና አሁንም 14 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝባችን ለረሀብ አደጋ ተጋልጦ እያለ መሬቶችን በኪራይ መልክ ለባዕዳን አሳልፎ መስጠት ወያኔ የሚዘርፈው በብዙ ሚሊዮን የሚገመት ብር ያስገኝለታል እንጂ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን ምንም የሚያስገኘው ጥቅም የለም። አገሪቷን ያዋርዳል ሕዝቧንም የበለጠ ችግርና መከራ ውስጥ ይከታል። ችግሩና መዘዙ ብዙ ነው። ከእርሻ መሬታቸው ወይም ለከብታቸው ግጦሽ ከሚሆነው መሬታቸው የሚፈናቀሉ ወገኖቻችን በርካታ ናቸው። በተለይ የአገራችን አርሶ አደር ከቀየው ተነስቶ የባዕድ አርሶ አደር (ቻይና አርሶ አደሮችን ለማሰማራት ዝግጅት ላይ እንደደሆነች ታውቋል) እንዲሰፍርበት ሲደረግ ምን ያህል ብሔራዊ ክብራችን እንደተዋረደ ማስተዋል ይቻላል። ባዕዳኑ በሠራተኛ መልክ የሚቀጥሩት ደሃው አርሶ አደር፥ የሚከፈለው በጣም አነስተኛ ገንዘብ በመሆኑ የሕዝባችን ጉልበት እየተበዘበዘ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ለባዕዳን የተሰጠው የእርሻ መሬት በተደጋጋሚ ስለሚታረስና ምንም ዓይነት እንክብካቤ ስለማይደረግለት ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ለምነቱን ያጣል። እንደ አበባ እርሻ የመሳሰሉት አዝርዕት እንዲሁም አለቁጥጥር ጥቅም ላይ የሚውለው ማዳበሪያ የመሬቱን ፍሬያማነት የሚያዳክሙና የሚያመክኑ መሆናቸው ከዚህ ቀደም ብሎ ተረጋግጧል። የአገሩና የመሬቱ ባለቤት የሆነው አርሶ አደሩ ጠባብ በሆኑና በቁርጥራጭ መሬቶች ላይ ተወስኖ ከእጅ ወደ አፍ የሆነ ኑሮ እንዲገፋ እየተገደደ ባለበት ሁኔታ ሰፋፊ መሬቶችን ለወጭ ባለሀብቶች በመስጠት የአርሶ አደሩን ጥቅም መጻረር፥ መብቱን ማፈን መሆኑ ሳይታለም የተፈታ ነው። በንጉሡ ጊዜ ተማሪዎችና ተራማጆች መሬት ለአራሹ ብለው እንዳልታገሉ ሁሉ ዛሬ ፀረ-ሕዝብና ፀረ ኢትዮጵያ የሆነው ወያኔ መሬት ለባዕዳን ሀብታሞች እያለ የአገሪቱን ሀብት በገፍ እየበዘበዘ መሆኑን ማየት አሳዛኝና ቁጭት ላይ የሚጥል ክስተት ነው። መሬት ለአራሹ የሚለው መፈክር ዛሬም በአርሶ አደሩ ፍላጎት ያልተሟላ መሠረታዊ ጥያቄ ነው።

አገራችን የአፈሯ ልማት፣ የውሃ ሀብቷና ተስማሚ የሆነው የአየር ንብረቷ የራሷን ሕዝብ ይቅርና ሌሎች አገሮችን በሚገባ ልትመግብ የሚያስችሏት ቢሆኑም ወያኔ ሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ ከረሃብና ከእልቂት ለመላቀቅ የማትችል መሆኑ ግልጽ ነው። ወያኔ ከራሱ ጥቅም በስተቀር የሚያስብ አይደለም። በሕዝብ ተመርጦ በትረ ሥልጣኑን የያዘ ስላልሆነም ለሕዝብ ተጠያቂነትን የሚፈራ አይደለም።

ድርቅ፥ ረሃብ፥ እልቂትና አምባገነንነት አንድ ላይ የሚሄዱ ናቸው። በነገራችን ላይ በድርቅም ሆነ ድርቅ በሚያስከትለው ረሃብና የሰው እልቂት በመሰቃየት በኩል አገራችን በዓለም ላይ የመጀመሪያ ወይም ብቸኛ አገር አይደለችም። በ19ኛው ምዕተ ዓመት የተለያዩ የአውሮፓ አገሮች በየጊዜው ድርቅ ገብቶ በተከሰተው ረሃብ በርካታ ሰዎች ሞተዋል። በ20ኛው ምዕተ ዓመትም እንደ ህንድ፥ ቻይና፥ ባንግላዴሽ፥ ቦትስዋና ወዘተ… በድርቅ ተጠቅተዋል። ብዙም ሰው አልቋል። በእነዚህና በሌሎች አገሮች ረሃብም ሆነ በረሃብ ምክንያት የሰው እልቂት ያቆመው የኢኮኖሚ እድገትና የፖለቲካ ሥርዓት ለውጥ ዕውን ከሆነ በኋላ ነው። ለሕዝብ ቅን አሳቢ የሆነ መንግሥት ሥልጣን በያዘበት ወይም የፖለቲካ ሥርዓቱ የሕዝብን ተጠያቂነት ባረጋገጠበት ሁኔታ ረሃብ ወይም የሕዝብ እልቂት አይኖርም።

ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በተዘረጋባቸው አገሮች ውስጥ ሕዝብ በእህል እጥረትና በረሃብ ሲሰቃይ የማይታይበት ዋናው ምክንያት በሕዝብ ምርጫ ሥልጣን የሚይዝ መንግሥት ተጠያቂነት ስላለበት የሚያቅደውና በተግባር ላይ የሚያውለው ፖሊሲ ዘወትር የሕዝብን ደህንነትና ጥቅም የሚያስቀድም በመሆኑ ነው። በፖሊሲ መዛባት ወይም በንዝህላልነት የመንግሥቱን ሥልጣን የጨበጠው ፓርቲ ሕዝብ ካስራበ÷ ከበደለ በቀጣዩ የምርጫ ዙር ከሥልጣን ይገለላል። ጥፋቱ ከፍ ያለ ከሆነም ባለሥልጣኖች ለፍርድ ቀርበው ቅጣታቸውን ያገኛሉ። በአምባገነን አገዛዝ ግን ይህ የሚታሰብ አይደለም። አምባገነኖች የሕዝብ መራብ ወይም በረሃብ ማለቅ ምንም የሚያሳስባቸውና የሚያስጨንቃቸው ባለመሆኑ የመከላከል እርምጃ ለመወሰድ የሚያስጨንቃቸው አይደለም። ችግሩ በገሃድ ሲከሰት ችግሩ አለ ብለው ለመቀመበል እንኳ ደንታ አይኖራቸውም። ስለዚህም ነው በ1966 ዓ.ም ወገኖቻችን በረሃብ ሲረግፉ ንጉሡና ባለሥልጣኖቻቸው ችግሩን ደብቀው የራሳቸውን ምቾትና ድሎት ሲያስፋፉ የነበሩት፤ ስለዚህም ነው በ1976 ዓ.ም በሚሊዮን የሚቀጠሩ ወገኖቻችን በረሃብ ሲሰቃዩ÷ ከሰውነት ጎዳና ሲወጡና ህይወታቸውን ሲያጡ የደርግ ቅብጤዎች 10ኛ ዓመት የፓርቲ በዓላቸውን ለማክበር በግብዣና በዘፈን ሲምነሸነሹና አስረሽ ምቺው ሲሉ የነበረው። ስለዚህም ነው አሁንም የረሃቡ ዳመና የበርካታ ወገኖቻችን ህይወት ለመቅጠፍ እያንዣበበ ባለበት ሰዓት የችግሩን ክብደት አሌ ብሎ ወያኔ በአሸናፊነት የሚወጣበትን የምርጫ ዘፈን እየዘፈነ ያለበትና የአገራችንን ምርጥ መሬቶች ለባዕዳን እየቸበቸበ የግል ካዝናውን በማደለብ ላይ የተሰማራው።

በዘመናችን በሀገራችን በድርቅ ምክንያት የተከሰቱት ሁለት አሰቃቂ እልቂቶች የደረሱት ለሕዝብ ደንታ በሌላቸው አምባገነን ሥርዓቶች ነው። አሁንም ሥልጣን ጨብጦ ያለው ቡድን በጥፋት ሥራ ከቀደሙት ሁለት አምባገነኖች በብዙ እጅ የሚበልጥ በመሆኑ ዘንድሮም በድርቅ ምክንያት ረሃብና ሌላ የጥፋት እልቂት ይከተላል ብለው የሚገምቱ ወገኖች ግምታቸው እምብዛም ከእውነት የራቀ አይደለም።

በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ረሃብና ድርቅ መንግሥትን ሲገረሰስ ላዲስ አምባገነን ሥርዓት ቦታውን ሲያመቻች አይተናል። የዛሬ 37 ዓመት የተከሰወተው ድርቅ የንጉሥ ኃይለ ሥላሴ ባላባታዊ ሥርዓትን አስወግዶ ለደርግ አገዛዝ ሁኔታውን አመቻቸ÷ የዛሬ 25 ዓመት የተከሰተው ድርቅ ደግሞ የደርግን መዳከም አፋጥኖ ከሰባት አመታት በኋላም ለወያኔ ቦታውን አለሳለሰ። በ1976 ዓ.ም ለተከሰተሰው ድርቅ የተሰጠውን የእርዳታ እህል ከሕዝቡ ጉሮሮ በመንጠቅ ሀብቱንና ጉልበቱን አዳብሮ ለሥልጣን የበቃው ወያኔ ደግሞ ዘንድሮ የሕዝባችንን ህይወት በገፍ ለመቅጠፍ አቆብቁቦ ያለውን ረሃብ ክብደቱን ለማቃለልና ለመደበቅ እያደረገ ባለው ተግባር ከሥልጣን የተወገደውን ደርግ ፈለግ እየተከተለ ነው። በአገራችን በስፋት ገብቶ ያለውን ረሃብ ክብደቱን እያቃለለና ዜናውን በምርጫና በሌሎች ጉዳዮች እንዲሸፍን እያደረገ የተለመደው የባዕዳን ምጽዋት እንኳን ትኩረት ተሰጥቶት በወቅቱና በሥነ ሥርዓት ለተራበውና ለተቸገረው እንዳይደርስ እንቅፋት እየሆነ ነው። ይህ የዚህን አምባገነን አገዛዝ ውድቀት ሊያፋጥን እንደሚችል ለብዙዎቻችን ግልጽ ቢሆንም ቀደም ባለው ጊዜ ያየ ቸው አሰቃቂ ትርዒቶች አሁንም ይደገሙ ይሆን ወይ የሚለው ፍርሃታችን ግን ከፍተኛ ነው።

ወያኔ ረሃብን አምራች÷ ችግርን ቀፍቃፊ ነው። ወያኔ በሥልጣን ላይ እስካለ ድረስ አገራችን ከድርቅም ሆነ ከችግር÷ ከረሃብም ሆነ ከእልቂት አዙሪት አትወጣም። ከዚህ መዓት ልትወጣ የምትችለው ዘረኛውንና አምባገነኑን የወያኔ የአገዛዝ ሥርዓት በማስወገድ በመሆኑ በተጠናከረ ትግል ተባብሮ ይህን ሥርዓት ማስወገዱ የኢትዮጵያውያን አገራዊ ግዴታ ነው።

በሕዝብ ትግል የወያኔ ሥርዓት ይገረሰሳል÷<br>
ረሃብና እልቂትን ለአንዴም ለሁሌም እናስወግዳለን።<br>
መሬት ለባለሀገሩ-ለአርሶ አደሩ!